## የወር አበባየ በማቆም ላይ/ማረጥ። የማህጸን ሴል/ህዋስ ምርመራ ያስፈልገኛልን?

አዎ፤ እድሜ ሲገፋ በማህጸን ጫፍ ላይ የነቀርሳ ችግር ስለሚከሰት ነው። ምንም እንኳን ከአንድ የወንድ ጓደኛ ጋር ብቻ የግብረስጋ ግንኙነት ቢያደርጉም፣ የወር አበባ ከቆመ በኋላም በየሁለት ዓመቱ የማህጸን ህዋስ ምርመራ ማድረጉ አስፈላጊ ነው።

## አንዳንድ ያልተለመደ የመድማት ሁኔታ አያለሁ

ያልተለመደ ደም ወይም ፈሳሽ ከእምስዎ ከወጣ በተቻለ ፍጥነት ሐኪሞትን ማየት ነው።

## ባለፈው የማህመን ሴል/ህዋስ ምርመራ ያደረኩበትን ጊዜ አላስተውስም

የሚቀጥለው የማህጸን ህዋስ ምርመራዎ ጊዜን ለማስታወስ የርስዎ ሐኪም ወይም የጤና ጥበቃ ክሊኒክ አሠራር ዘዴ ሊኖራቸው ይችላል። የርስዎ የማህጸን ህዋስ ምርመራ ውጤት ሲመዘገብ በእያንዳንዱ መስተዳድርና ተሪቶሪ የስም ዝርዝር ይኖረዋል። ለሚቀጥለው የማህጸን ህዋስ ምርመራ ወይንም ተከታታይ የሆነ ህክምና ካለ ጊዜው ሲቃረብ የማስታወሻ ደብዳቤ ይላክልዎታል። የርስዎ መረጃ በስም ዝርዝር ውስጥ እንዳይመዘገብ ወይም የማስታወሻ ደብዳቤ ካልፈለጉ ለሐኪምዎ መናገር ነው።

## የማህጸን ሴል/ህዋስ ምርመራ ማድረግ የምችለው የት ነው?

በአካባቢዎ ከሚገኝ ሐኪምዎ፣ ነርስ ወይም የወሊድ መቆጣጠሪያ ክሊኒክ ቀጠሮ ማቀናጀት ይችላሉ። የርስዎን ማህጸን ህዋስ ምርመራ ለማድረግ የሴት ሐኪም ወይም ነርስ መጠየቅ ይችላሉ። አስተርጓሚ እንዲገኝ ከፈለጉ ቀጠሮው በሚቀናጅበት ጊዜ ይናገሩ። እንዲሁም ጓደኛ ወይም ከርስዎ ጋር የቤተሰብ አባል ቢወስዱም ጥሩ ነው።

## የማህጸን ጫፍን ነቀርሳ ሊከላከል ስለሚችል አዲስ ክትባት ሰምቻለሁ

አዎ፣ አብዛኛውን ለHPV አይነት ማህጸን ጫፍ ነቀርሳ መንስዔ የሚሆንን ቁስለት ለመከላከል ይቻል ዘንድ ክትባት ይቀርባል። በአውስትራሊያ ውስጥ እድሜያቸው ከ9 እስከ 26 ዓመት ለሆኑ ሴቶች ክትባቱ ይፈቀዳል።

በአገር አቀፍ የበሽታ መከላከያ ፕሮግራም በኩል HPV ክትባት በነጻ ይሰጣል።

ወጣቶች የግብረስጋ ግንኙነት ከመጀመራቸው በፊት ክትባቱ ቢሰጣቸው የበለጠ ይሆናል። የክትባቱ ዓላማ ለወደፊት ትውልድ ከሴቶች ማህጸን ጫፍ ነቀርሳ ለመከላከል ይሆናል። እድሜዎ ከ12 እስከ 26 ዓመት ወይም እድሜዋ ከ12 እስከ 26 ዓመት የሆናት ሴት ልጅ ካለዎ ስለ ክትባት አጀማመር ለሐኪምዎ ያነጋግሩ።

ክትባቱ ለማህጸን ጫፍ ነቀርሳ ምክንያት ከሚሆኑት አንዳንዶቹን HPV ስለሚከላከል ታዲያ ሁልጊዜ የማህጸን ህዋስ ምርመራ ማካሄድ አስፈላጊ ነው።

**ለማህጸን ጫፍ ነቀርሳ ምክንያት የሆኑትን ሁሉንም HPV አይነት በክትባት መከላከል ስለማይቻል ሁልጊዜ የማህጸን ህዋስ ምርመራ ማካሄድ አስፈላጊ ይሆናል።**

ስለ HPV እና ክትባት በበለጠ መረጃ ለማግኘት በአውስትራሊያ የክትባት ፕሮግራም ድረገጽ **www.immunise.health.gov.au** ላይ ይቀርባል።

**ከማህጸን ጫፍ ነቀርሳ ለመከላከል ሁልጊዜ የማህጸን ህዋስ ምርመራ ማካሄድ ነው።**

ስለማህጸን ህዋስ ምርመራ ማድረግ ለበለጠ መረጃ ወይም በመስተዳድሩ ወይም ተሪቶሪ ካለው የማህጸን ህዋስ ምርመራ መዝገብ ስምዎን ለማሰረዝ ወይም ወቅታዊ ለማድረግ ከፈለጉ በስልክ 13 15 56 ደውሎ ማነጋገር (በአካባቢ ስልክ)።

በእንግሊዝኛ ለመነጋገር ችግር ካለብዎ የትርጉምና አስተርጓሚን በስልክ 13 14 50 መደወል ነው። ይህ ክፍያ በአካባቢ የስልክ ጥሪ ሂሳብ ይሆናል።

በተጨማሪም በእኛ ድረገጽ **www.cancerscreening.gov.au** ላይ መጎብኘት።

AMHARIC



# ባለፈው መቼ ነው የማህጸን ህዋስ ምርመራ ያካሄዱት?

እያንዳንዱ ሴት በየሁለት ዓመቱ የማህጸን ህዋስ ምርመራ ካካሄዱ አብዛኛውን የማህጸን ጫፍ ነቀርሳ ለመከላከል ይቻላል።

**National Cervical Screening Program**

በአውስትራሊያ፣ መስተዳድርና ተሪቶሪ መንግሥት በጋራ አነሳሽነት የወጣ

ምክንያት ባለመፍጠር ቀጠሮ ማቀናጀት ይሆናል

## የማህጸን ህዋስ ምርመራ ምንድ ነው?

ይህ የርስዎ ማህጸን ጫፍ ጤናማ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚደረግ ምርመራ ነው። ይህ ማህጸን የሚከፈትበትና ከላይኛው እምስዎ ላይ ይገኛል (ከዚህ በታች ያለውን ስእል ይመልከቱ)።

የማህጸን ህዋስ ምርመራን ለማካሄድ ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ የሚወስድና አያምም።

የማህጸን ጫፍ ነቀርሳን ለመከላከል በየሁለት ዓመቱ የማህጸን ህዋስ ምርመራ ማካሄዱ የበለጠ ዘዴ ይሆናል።




## ማህጸን ህዋስ ምርመራ ለምንድ ነው?

ይህ የማህጸን ጫፍ ነቀርሳ ከመፈጠሩ በፊት ቀደም ብሎ ማስጠንቀቂያ መስጠት ስለሚችል ነው። አንዳንድ ጊዜ የማህጸን ጫፍ ህዋስ ከጤናማ ወደ ጤናማ አለመሆን ስለሚቀየር ነው። ከማህጸኑ ጫፍ ወደ ነቀርሳ ከመለወጡ በፊት በህዋሱ ላይ ያልተለመደ ሁኔታ ሊታይ ይችላል።

## ለማህጸን ጫፍ ነቀርሳ መንስሄው ምንድ ነው?

አብዛኛው የማህጸን ጫፍ ነቀርሳዎች የሚመጡት HPV (human papillomavirus) በተባለ ቫይረስ መበከል ይሆናል። ከ100 በላይ የሚሆኑ የተለያየ HPV ቫይረስ አይነቶች እንዳሉ ነው። ከነዚህ አይነቶች ቫይረሶች ውስጥ ሁለቱ በአውስትራሊያ ለአብዛኛው የማህጸን ጫፍ ነቀርሳዎች ምክንያት መሆናቸው ይታወቃል።

HPV ቫይረስ በጣም የታወቀ ነው። አብዛኛው ህዝብ (ከአምስት አራቱ) የHPV ቫይረስ በሕይወታቸው ጊዜ ውስጥ ያጋጥማቸዋል። ማንኛውም ሰው የግብረስጋ ግንኙነታ ካደረገ HPV ቫይረስ ሊኖርበት ይችላል።

በአብዛኛው ጊዜ HPV ቫይረስ ከጥቂት ዓመታት በኋላ በራሳቸው ይጠፋሉ። አንዳንድ ጊዜ ቫይረሱ በሰውነትዎ ውስጥ ለብዙ ጊዜ ሊቆይ ሲችል ታዲያ ወደ ማህጸን ጫፍ ነቀርሳ ሊያመጣ ይችላል። ብዙጊዜ እስከ 10 ዓመታት የሚሆን ጊዜ ሊወስድ ይችላል።

በየሁለት ዓመት የማህጸን ህዋስ ምርመራ ማካሄዱ HPV ቫይረስ ወደ ነቀርሳ ከመቀየሩ በፊት በህዋሱ ላይ ለውጥ እንዳለ ለማወቅ ይቻላል። ታዲያ በርስዎ ሐኪም፣ ነርስ ወይም የጤና ሠራተኛ ጤንነትዎ በቁጥጥር ስር ስለመሆኑ በማረጋገጥና አስፈላጊም ከሆነ ህክምና በማግኘት ጤናማ ሆነው መቆየት እንዲችሉ ያረጋግጣሉ።

## የማህጸን ህዋስ ምርመራ የሚያስፈልገው ማን ነው?

እድሚያቸው በ18 እና 70 ዓመት ያሉ ሴቶች በሞላና የግብረስጋ ግንኙነት የሚያደርጉ በየሁለት ዓመቱ የማህጸን ህዋስ ምርመራ ማድረግ አለባቸው። ምንም እንኳን የግብረስጋ የሚፈጽሙት ከባልዎ ጋር ቢሆንም ሁልጊዜ የማህጸን ህዋስ ምርመራ ማድረግ አለብዎት።

## ማህጸኔን ለማውጣት ቀዶ ጥገና ባደርግስ (hysterectomy) ምን ይፈጥራል?

በአካሄዱት የማህጸን ቀዶ ጥገና አይነት፣ አሁንም ቢሆን የማህጸን ህዋስ ምርመራ ሊያስፈልግዎ ይችላል። እርስዎ በበለጠ ምን እንደሚያስፈልግዎ ለርስዎ ሐኪም፣ ነርስ ወይም የጤና ሠራተኛ ማነጋገር ነው።

## እንዴት የማህጸን ህዋስ ምርመራ ይደረጋል?






## የሚሆነው እንዲህ ነው...

ሐኪምዎ ምርመራውን ለማካሄድ በመጀመሪያ በጀርባዎ ገደም እንዲሉና ከዳሌዎ በታች ያለውን ልብስ እንዲያወልቁ ይጠየቃሉ። የሴት ሐኪም እንድትሆንልዎ መጠየቅ ይችላሉ። ከዚያም ሐኪም የርስዎን እምስ ለመክፈት የማስፊያ መሳሪያ በመጠቀም፣ ስለዚህ የማህጸኑ ጫፍ በበለጠ ግልጽ ሆኖ ሊታይ ይችላል።

የርስዎን ማህጸን ቀስ አድርጎ በትንሽ ብሩሽ ወይም መሰቅሰቂያ (በትንሽ ፕላስቲክ ወይም ስንጥር እንጨት) አድርጎ አንዳንድ ህዋስ/ሴሎችን ጥራጊ መውሰድ። ታዲያ ሴሎችን በመስታወት ፊልም ማሳያ ላይ በማድረግ በማይክሮስኮፕ እንዲታዩ ወደ ላቦራቶሪ መላክ ይሆናል።

## ስሜቱ ምን ይመስላል?

አንዳንድ ጊዜ የማህጸን ህዋስ ምርመራ ለማካሄድ ትንሽ ሊያሳፍር ይችላል። ያስተውሉ፣ ይህንን ምርመራ ለሚያካሂድ ሰው የቀን ተቀን ሥራቸው ስለሆነ አያሳፍራቸውም።

የአሰራር ሂደቱ ትንሽ ላይመች ይችላል ነገር ግን ሊያም አይችልም። ይሁን እንጂ ሲያምዎት ለርስዎ ሐኪምን ነርስ ወይም የጤና ሠራተኛ ወዲያውኑ መናገር ነው። መናገርና ልርሐኪም አያምም።

## ስለ ውጤቱስ?

የማህጸን ህዋስ ምርመራ ሲያካሂዱ ውጤቱን መቸና እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ለሐኪም መጠየቅ አስፈላጊ ነው።

**አብዛኛው ውጤት ጤናማ ይሆናል**

## የእኔ ምርመራ ውጤቶች ትክክል ካልሆኑ ምን ይደረጋል?

የምርመራ ውጤትዎ ጤናማ ካልሆነ ታዲያ ይህ ማለት ነቀርሳ አለብዎ ማለት አይደለም። ብዙጊዜ ይህ ሲከሰት የሆነ ቀላል እንደ ቁስለት አለብዎ ማለት ሲሆን ታዲያ እራሱ በተፈጥሮ ይጠፋል።

አንድ ሴት የማህጸን ህዋስ ምርመራ በተደጋጋሚ ለማድረግ ያስፈልጋት ይሆናል። አንዳንድ ያልተለመደ የህዋስ/ሴሎች አይነት በልዩ ባለሙያ በኩል መታከም ይኖርባቸው ይሆናል። ለርስዎ የበለጠው የትኛው ስለመሆኑ ከርስዎ ሐኪም፣ ነርስ ወይም የጤና ሠራተኛ በማነጋገር ማረጋገጥ።